የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ፍራንክፈርት 26. APRIL 2016

# የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ

ግንባታ የተጀመረበት 5ኛው አመት ክብረ በዓል በሽቱትጋርት ከተማ በደማቅ ሁኔታ ተከበረ፣

## የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የተጀመረበት 5ኛው አመት ክብረ በዓል በሽቱትጋርት ከተማ በደማቅ ሁኔታ ተከበረ፣



ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረተ ድንጋይ የተጣለበት 5ኛ አመት በሽቱትጋር ከተማ በአከባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፡፡በእለቱ የፕሮግራሙ የክብር እንግዳ የሆኑት በፍራንክፈርት



የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ቆንስል ጄኔራል አቶ ምህረተአብ ሙሉጌታ የግድቡ ግንባታ የደረሰበትን ደረጃ ገለፃ ያደረጉ ሲሆን፣ በገለፃቸው ላይ „ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በይፋ ከተበሰረበት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም. አንስቶ በከፍተኛ ህዝባዊ ድጋፍ በመገንባት ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ ግድቡ ከሚያስገኘው ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል በላይ መላው ኢትዮጵያውያንን ያለምንም ልዩነት ባንድ ጥላ ስር በማሰባሰቡ በሀገራችን በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ብሄራዊ መግባባትን መፍጠሪያና ሀገራዊ አንድነትን ማጠናከሪያ ከመሆኑም በላይ የይቻላል መንፈስ ተላብሰን ታላላቅ ልማቶችን እንድንደፍር በማድረጉ የሀገራችንን በጎ ገፅታ በመገንባት ረገድ የበኩሉን ታላቅ ሚና እየተወጣ እንደሚገኝና  በዚህም ምክንያት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለተያያዝነው የህዳሴያችን ጉዞ ፋና ወጊ፣ የሀገራችን ብሄራዊ ኩራት፣የማንነታችን መገለጫ ብለን የምንገልፀው ብለዋል“፡፡ በመቀጠልም ቆንስል ጄኔራሉ ለዘመናት አንገታችንን ዝቅ እንድናደርግና በአገር ውስጥም ሆነ በውጪው አለም እንድናፍርና እንድንሸማቀቅ ያደረገንን ድህነት በማስወገድ፣ የተጀመረውና አበረታች ውጤት እያሳየ ያለውን የህዳሴው ጉዞ እውን ይሆን ዘንድ በሽቱትጋርትና አከባቢው ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እያደረጉት ያሉት ድጋፍና ተሳትፎ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ የዳያስፖራው አባላትም በበኩላቸው ምንም አይነት ልዩነት ሳይገድባቸው እየተካሄደ ባለው የልማት እንቅስቃሴ በመሳተፍ የህዳሴው ጉዞ አካል መሆን አማራጭ የሌለውና፣ ልማትን መቃወም ከአገርና ህዝብ መካድ ተለይቶ እንደማይታይ ገልፀዋል፡፡
በቦንድ ግዥና ስጦታ መልክ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል 670000 ብር የተሰበሰበ ሲሆን፣ የግድቡ ግንባታ እስከ ሚጠናቀቅ ድረስም ገቢ የማሰባሰቡ ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ቃል ተገብቷል፡፡

ከሰላምታ ጋር
ምስግና ተክሉ
የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቆንስል

